STAY SAFE MN

# የ COVID-19 ምርመራ ውጤት በመጠባበቅ ላይ እያሉ ምን እንደሚያድረጉ

## ከተመረመሩ በኋላ

- በቤትዎ ይቆዩ እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ይራቁ፣ በተለይ ምልክቶች ካልዎት። ምንም እንኳን የህመም ምልክት ባይኖርዎትም በቤትዎ መቆየት ተመራጭ ነው፣ የግድ መውጣት ካስፈለግዎ ግን ማስክ ያድርጉ እንዲሁም ከሌሎች 6 ጫማ ይራቁ።
- የምርመራው ውጤት ፖዘቲቭ ከሆነ እቅድ ማውጣት ይጀምሩ ምክንያቱም በቤትዎ ቢያንስ ለ10 ቀናት መቆየት ይኖርብዎታል።
- በቅርብ ጊዜ ያገኟቸውን ከእርስዎ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች ዝርዝር ያዘጋጁ። COVID-19 ሊኖርብዎ እንደሚችል ይንገሯቸው እንዲሁም የእርስዎን ውጤት እስከሚሰሙ ድረስ ከሌሎች መራቅ አለባቸው።
- የተመረመሩት COVID-19 ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት የነበርዎ ከሆነ እና ምንም ምልክት ከሌለብዎ የምርመራ ውጤትዎን እስኪያውቁ ድረስ በቤትዎ መቆት አለብዎ እንዲሁም የምርመራ ውጤትዎ ኔጌቲቭ ቢሆንም እንኳን አሁንም ሊታመሙ ስለሚችሉ ለ14 ቀናት በቤትዎ መቆየት ይኖርብዎታል።
- የተመረመሩት ለሌላ ህክምና ሂደት ከሆነ እና ምንም ምልክት ከሌለብዎ የምርመራውን ውጤት እስኪያውቁ ድረስ በቤትዎ መቆየት አይጠበቅብዎትም።
- የምርመራ ውጤትዎን እስኪያውቁ የተወሰነ ቀን ሊወስድ ይችላል። የምርመራ ውጤትዎን በኢ-ሜይል፣ አጭር የፅሁፍ መልእክት ወይም በስልክ እናሳውቅዎታለን።
- የበሽታ ምልክትዎን ይቆጣጠሩ። ምልክትዎ ከጨመረ የህክምና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግረሩ። የCOVID-19 ምርመራ አድርገው እንደነበረ ይንገሩ።

## ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ

- ይሄ ማለት COVID-19 አለብዎ ማለት ነው።
- በቤትዎ ይቆዩ። የማህበረሰብ ጤና ሰራተኛ ይደውልልዎታል። ስልክ በሚደውሉበት ጊዜ መመለስዎ አስፈላጊ ነው። ለCOVID-19 ስላልዎት ተጋላጭነትበቀጥታ ያገኟቸውን ሰዎች እና የሄዱባቸውን ቦታዎች አይነት ጥያቄዎች ይጠይቁዎታል ።
- በተጨማሪም ምን ማድረግ እንዳለብዎት እና በቤትዎ ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለብዎት ተጨማሪ መረጃ ይሰጡዎታል።

## ውጤትዎ ኔጌቲቭ ከሆነ

- ይሄ ማለት አሁን COVID-19 የለብዎትም። ሆኖም ግን ተጋላጭ ሊሆኑ ወይም በማንኛውም ጊዜ ሊታመሙ ይችላሉ ። እራስዎን እና ሌሎችን ከCOVID-19 ለመጠበቅ እርምጃዎች መውሰድዎን መቀጠል አለብዎት።
- የCOVID-19 ምልክቶች ከታየብዎ እንደገና ለመመርመር ከዶክተርዎ ወይም ከሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ጋር ይነጋገሩ።

## ተጨማሪ መረጃ

Minnesota Department of Health's COVID-19 ድረ-ገፅ (www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/)

**Minnesota Helpline 651-297-1304 or 1-800-657-3504**
(ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋት 9 ሰአት እስከ ከሰአት 4 ሰአት)

MINNESOTA

Minnesota Department of Health | health.mn.gov | 651-201-5000
አማራጭ አቀራረብ ለመጠየቅ health.communications@state.mn.us ያግኙ።

8/24/2020 (Amharic)